ዜና
አመዝኮ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣ ቅፅ 11 ቁጥር 5 ነሐሴ 1997

# በኢትዮጵያ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ምላሽ አቅም እየጎለበተ መምጣቱ ተገለፀ

በኢትዮጵያ በተለያዩ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ሰብዓዊ ችግር ለሚገጥማቸው ወገኖች አስፈላጊውን ሰብዓዊ ዕርዳታ በወቅቱ በማቅረብ ረገድ በአሁኑ ጊዜ ያለው አቅም ከሦስትና አራት ዓመታት በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር እየጎለበተ እና እየተጠናከረ መጥቶ ከምንጊዜውም በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተገለፀ።



ይኸ የተገለፀው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የአፍሪካ ቀንድ ሰብዓዊ ጉዳዮች ልዩ መልዕክተኛ የሆኑት ሚስተር ማርቲ አህቲሳሪ ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ ጋር በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ባለው ሰብዓዊ ዕርዳታና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ነሐሴ 20 ቀን 1997 ዓ.ም በተወያዩበት ወቅት ነው። በዚሁ ውይይት ላይ ሚስተር አህቲሳሪ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋዎች ተጠቂ ለሚሆኑ ሰዎች አስፈላጊ ሰብዓዊ ዕርዳታዎችን በወቅቱ በማቅረብ ረገድ ያለው አቅም ጉልህ ሊባሉ የሚችሉ መሻሻሎች ታይተውበታል ፤ የታዩትን መሻሻሎችም መንግሥት ፣ ለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች በጋራ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ይበልጥ ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል። በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተጀመሩ ሥራዎች ላይ በቁርጠኝነት በመረባረብ ከግብ ለማድረስ መጣር እንደሚያስፈልግም ሚስተር አህቲሳሪ ተናግረዋል።

በማያያዝም የምግብ እጥረት በሚያጋጥምባቸው አካባቢዎች በችግሩ ይበልጥ ተጠቂ የሆኑትን ህፃናትና እናቶች ለመታደግ በማሰብ የተጀመረው የአደጋ ጊዜ ልዩ የሥርዓተ ምግብ አቅርቦት ስትራቴጂ **(Emergency out reach Strategy)** በአወንታዊ መልኩ ከሚጠቀሱት የአሠራር ማሻሻያዎች በዋንኛነት ሊቀጥል የሚችልና ይበልጥ ተጠናክሮና በሁሉም ክልሎች ተስፋፍቶ ሊጠቀስ የሚገባው መሆኑን ጠቅሰዋል። ከዚሁ ጋርም የአስቸኳይ ጊዜ ሥርዓተ ምግብ አቅርቦትን ለማስተባበር በአመዝኮ ውስጥ የተቋቋመው የአስቸኳይ ጊዜ ሥርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ የዩኒት በሰው ሀይልና አስፈላጊ ቁሳቁስ መጠናከር እንደሚገባው ሚስተር አህቲሳሪ ጠቅሰዋል።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ በበኩላቸው በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ከሰብዓዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ያለው ሁኔታ መረጋጋት የሚታይበትና አስፈላጊ ሰብዓዊ ዕርዳታዎችም በወቅቱ እየቀረቡ መሆኑን ጠቅሰው ፣ በዚህ ረገድ ለጋሽ ሀገራት ለዚህ አመት ከሚያስፈልገውና ለመስጠት ቃል ከገቡት የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እስካሁን 95 በመቶ ያህሉን ለመስጠት ቃል የገቡና የለገሡ በመሆናቸው ያጋጠመ የጎላ ችግር አለመኖሩን አስረድተዋል።

## በዚህ እትም ውስጥ

**የኮምቦልቻ ማዕከላዊ መጋዘን በበጀት ዓመቱ ከ922 ሺህ ኩንታል በላይ የዕርዳታ እህል ወደ ክልሎች ማጓጓዙ ተገለፀ**
በፌዴራል አመዝኮ የኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘን በ1997 በጀት ዓመት 922 ሺህ 349 ኩንታል የዕርዳታ እህል በአማራ ፣ በአፋርና በትግራይ ክልሎች ለሚገኙ 470 የማከፋፈያ ጣቢያዎች ማጓጓዙን አስታወቀ።
*ገጽ 2*

**ድርጅቶቹ የልማት አጋርነታቸውን በማሳየት ላይ ናቸው**
በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የልማት አጋርነታቸውን በማሳየት ላይ መሆናቸውን አቶ ሀሰን መሀመድ ገለጹ።
*ገጽ 3*

**ወርልድ ቪዥንና ድጋፍ ለዘላቂ ልማት በአፋር የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው**
በአፋር ክልል ወርልድቪዥን ኢትዮጵያና ድጋፍ ለዘላቂ ልማት የተባሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የአዋሽና የአውራ ወንዞችን በመጥለፍ የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ የሚያስችሉ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው።
*ገጽ 4*

**ድርጅቶቹ ከ172 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ካፒታል ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው**
በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ቁጥራቸው 28 የሚሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከ 2003 እስከ 2007 የሚቆዩ ልዩ ልዩ የግብርና እና የገጠር ልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኙ ተገለጸ።
*ገጽ 5*

**ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶች የአጠናን ስልት ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሄደ**
*ገጽ 6*

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት
ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት
የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ ፡ **www.dppc.gov.et**

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹን የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሌሎች ተጎዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

በማያያዝም ኮሚሽነሩ በአሁኑ ጊዜ ያለው የአደጋ ምላሽ አቅም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱን ይበልጥ በማጠናከር በመረጃ ልውውጥ፣ ከለጋሽና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅርበት በመሥራት፣ የሚፈለገውን ዕርዳታ ከለጋሽ ሀገራት በወቅቱ በማግኘትና ዕርዳታውን ለተረጂው ህዝብ ለማድረስ በሚደረግ እንቅስቃሴ ረገድ ባለፉት ዓመታት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል:: ይኸም ወደፊት ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ያላቸውን እምነት ገልፀዋል::

የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድም መንግሥት በነደፋቸው ስትራቴጂዎች አማካይነት እየተከናወኑ ባሉት በርካታ ሥራዎች አበረታች ውጤቶች መታየታቸውን ኮሚሽነር ሲሞን ጠቁመው፣ በዚህ ረገድ ለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ ዘርፎች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል ስላልሆነ ከመንግሥት ጋር በቅርበት መሥራት እንደሚገባቸው አመልክተዋል::

በመጨረሻም ሚስተር አህቲሳሪ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ዓይነተኛ ግባቸው ሰብዓዊ ችግሮችን ማቃለል እና ብሎም ማስወገድ በመሆኑ በአስቸኳይ የሰብዓዊ ዕርዳታ እንቅስቃሴዎችም ሆነ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚሰሩ ሥራዎች ሁሉ ከአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኮሚሽንና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በቅርበት በመስራት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውንም አረጋግጠዋል::

## የኮምቦልቻ ማዕከላዊ መጋዘን በበጀት ዓመቱ ከ922 ሺህ ኩንታል በላይ የዕርዳታ እህል ወደ ክልሎች ማጓጓዙ ተገለፀ

በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘን በ1997 በጀት ዓመት 922 ሺህ 349 ኩንታል የዕርዳታ እህል በአማራ ፣ በአፋርና በትግራይ ክልሎች ለሚገኙ 470 የማከፋፈያ ጣቢያዎች ማጓጓዙን አስታወቀ::

የማዕከላዊ መጋዘኑ ኃላፊ አቶ መኩሪያ ጓንጉል በሥፍራው ለተገኘው የፌዴራል አመዝኮ የሕዝብ ግንኙት ቡድን እንደገለጹት በአንድ ጊዜ 200 ሺህ ኩንታል የመያዝ አቅም ባለው በዚሁ መጋዘን በየጊዜው ከውጭ ዕርዳታና እንደዚሁም በአገር ውስጥ ግዥ የሚገባውን የዕርዳታ እህል በመከታተል ከዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ በሚቀርበው መጠየቂያ መሠረት ለትግራይ ፣ ለአማራና ለአፋር ክልሎች ወጭ እንደሚደረግ ገልፀው ፣ በበጀት ዓመቱ በ4 ሺህ 510



ተሸከርካሪዎች የዕርዳታ እህሉን ማጓጓዙን አመልክተዋል::

ከወደብ ወደ መጋዘኑ የሚራገፍና ከመጋዘኑ ወደ ዕርዳታ ማሠራጫ ጣቢያዎች የማጓጓዝ ሥራ በሚጨምርበት ጊዜ እስከ 3 ሺህ አውራጅና ጫኝ ሠራተኞችን እንደሚሠማሩም አመልክተዋል::

ኮሚሽኑ ለአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦት የሀገሪቱን መልከዓምድር አቀማመጥ ከግምት ከማስገባት ካቋቋማቸው ሦስት ማዕከላዊ መጋዘኖች አንዱ የኮምቦልቻው መሆኑን ጠቅሰው ይኸው መጋዘን በሰሜኑ የአገራችን ክልል ለአማራ ፣ ለትግራይና ለአፋር አካባቢዎች የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግር ለደረሰባቸው ወገኖች የተለያዩ አስቸኳይ ዕርዳታ ለማከማቸትና ለማሰራጨት ታስቦ በ1978 ዓ.ም መቋቋሙንም አስታውሰዋል::

## ድርጅቶቹ የልማት አጋርነታቸውን በማሳየት ላይ ናቸው

በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የልማት አጋርነታቸውን በማሳየት ላይ መሆናቸውን አቶ ሀሰን መሀመድ በአፋር ክልላዊ መንግሥት የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና ምግብ ዋስትና ቢሮ ሃላፊ ገለጹ::

ኃላፊው ሰሞኑን ወደ ሥፍራው ለተንቀሳቀሰው የፌዴራል አመዝኮ የሕዝብ ግንኙነት ቡድን እንደገለጹት በአሁኑ ጊዜ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚቆይ ከ93 ሚሊዮን ብር በላይ የፕሮጀክት ስምምነት ከቢሮውና ሴክተር መ/ቤቶች ጋር ተፈራርመው ሕብረተሰቡ በውሃ፣ በጤና ፣ በትምህርት ፣ በገጠር እርሻ ልማት ረገድ ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸው የልማት አጋርነታቸውን ያመለክታል ብለዋል::

ከሌሎች ክልሎች አንፃር ሲታይ በአፋር ክልል የሚንቀሳቀሱት 24 መያዶች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም ፣ ያሉትንም ለማስተባበር የሚያስችል በክልሉ የተሟላ አቅምና መመሪያ ቀደም ሲል ስላልነበር ለክትትልና ቁጥጥር አስቸጋሪ ነበር ያሉት ኃላፊው በአሁኑ ወቅት ከፌዴራል አመዝኮ በተገኘው ልምድና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ አንድ መመሪያ ተዘጋጅቶና ተጠናቆ እንዲፀድቅ ለሚመለከተው አካል መቅረቡን አስታውቀዋል::

በክልሉ ከሚንቀሳቀሱት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሕብረተሰቡን በእርሻ ዘርፍ በመስኖ ሰብል የማምረት ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ በማልማትና የዶሮ እርባታ በማለማመድ ተጠቃሚ ለማድረግ ሁነኛ ሥራ በመሥራት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ እንደሚገኙ የገለጹት አቶ ሀሰን ይህም የአፋር ህብረተሰብ የሥራ ባህሉ ያልዳበረ ነው የሚለውን አባባል የሚለውጥ ነው ብለዋል::

አያይዘውም ክልሉ በብዙ መልኩ የአቅም ውስንነት ቢኖርበትም ፣ የህብረተሰቡ የልማት ፍላጎት ከምንጊዜውም በላይ እየጨመረ በመምጣቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በልማት አጋርነት በመመልከት ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ያሉት ኃላፊው የአቅም ውስንነታችንን ለማስወገድ በሎጂስቲክስም ሆነ በሥልጠና ረገድ የፌዴራል አመዝኮ ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል::



መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚቆይ ከ93 ሚሊዮን ብር በላይ የፕሮጀክት ስምምነት ከአደጋ መከላከል ዝግጁነትና ምግብ ዋስትና ቢሮና ሴክተር መ/ቤቶች ጋር ተፈራረሙ ሕብረተሰቡ በውሃ፣ በጤና ፣ በትምህርት ፣ በገጠር እርሻ ልማት ረገድ ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ በመንቀሳቀስ ላይ ነው::

# ወርልድ ቪዥንና ድጋፍ ለዘላቂ ልማት በአፋር የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው



ወ/ሮ ሀዋ አብደላ የተባሉ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ በበኩላቸው እንደገለጹት ከድርጅቱ ባለሙያዎች በተሰጣቸው ምክር ተጠቅመው እንደ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም ፣ ቃሪያና በርበሬ በጓሯቸው በመትከል የቤት ውስጥ የምግብ ፍጆታቸውን ከመሸፈን አልፈው ገበያ አውጥተው በመሸጥ ከ300 ብር በላይ ገቢ ማግኘታቸውን ገልፀዋል::

ወርልድቪዥን ኢትዮጵያና ድጋፍ ለዘላቂ ልማት /**Support for sustainable Development**/ የተባሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት 14 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ፕሮጀክት በመቅረፅ የአዋሽና የአውራ ወንዞችን በመጥለፍ የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ የሚያስችሉ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው::

የድርጅቶቹ የፕሮግራም አስተባባሪv ሰሞኑን ወደ ሥፍራው ለተንቀሳቀሰው የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ቡድን እንደገለጹት የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ የሚያስችሉ በ14 ሚሊዮን 840 ሺህ 891 ብር ካፒታል በቀረጹት የልማት ፕሮጀክቶች የአዋሽና የአውራ ወንዞችን በመጥለፍ አርብቶ አደሩን የመስኖ ተጠቃሚ በማድረግ በተለምዶ ከሚያከናውነው የእንስሳት ዕርባታ ጎን ለጎን አትክልት ፣ ፍራፍሬና ሰብል ማምረትን እንዲለማመድ በማድረግ ውጤታማ ሥራ በመሥራት ላይ ናቸው::

አቶ እንዳለ ለማ የወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ የአፋር አካባቢ ልማት ፕሮግራም አስተባባሪ እንደገለጹት ድርጅቱ እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም በክልሉ በተከሰተው ድርቅ ሣቢያ የዕለት ዕርዳታ ፕሮግራሞችን ለማካሄድ ወደ ክልሉ እንዳገባ አስታውሰው፣ እ.ኤ.አ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአሳይታ ወረዳ የአዋሽ ወንዝን በመጥለፍ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የ12 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ቀርጾ በአሁኑ ጊዜ ሕብረተሰቡን በአትክልትና ፍራፍሬ ፣ በጓሮ አትክልትና በሰብል ማምረት ሥራ እንዲሰማራ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው::

ወ/ሮ ሀዋ አብደላ የተባሉ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ በበኩላቸው እንደገለጹት ከድርጅቱ ባለሙያዎች በተሰጣቸው ምክር ተጠቅመው እንደ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም ፣ ቃሪያና በርበሬ በጓሯቸው በመትከል የቤት ውስጥ የምግብ ፍጆታቸውን ከመሸፈን አልፈው ገበያ አውጥተው በመሸጥ ከ300 ብር በላይ ገቢ ማግኘታቸውን ገልፀዋል::

ድርጅቶቹ በደን ልማት ረገድም የድሬደዋ ዛፍ ተብሎ የሚጠራውን ችግኝ በአሳይታ ወረዳ



በሄነሌ ቀበሌ የችግኝ ጣቢያ በማቋቋም 33 ሺህ ችግኞችን በማራባት ለ6 የህብረት ሥራ ማህበራት ማከፋፈሉን አቶ እንዳለ አስረድተዋል::

ከዚህም ሌላ ድርጅቱ ህብረተሰቡን የውሃ ሀብት ተጠቃሚ ለማድረግ በአሣይታ ወረዳ ለ12 ዓመት ያህል ውሃ ባልደረሰበት የጋሃርቱ ቀበሌ 365 ሜትር ኩብ ውሃ የሚይዝ ኩ

መገንባቱንና የውኃ ማስተላለፊያ ገንዳ መሥራቱንም ገልፀዋል::

በተመሳሳይ ሁኔታ ድጋፍ ለዘላቂ ልማት /**Support for sustainable Development**/ የተሰኘው አገር በቀል መንግሥታዊ ያለሆነ ድርጅት የ2 ሚሊዮን 840 ሺህ 891 ብር ፕሮጀክት በመቅረፅ ሥራዎችን በማከናወን አርብቶ አደሮች የሰብል ምርቶችን በመዝራት እንዲለማመዱ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ገልፀው ፣ 10 ዓይነት የጓሮ ዘሮችን በአካባቢው በማራባት ከበቆሎ በተጨማሪ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን እንዲያለሙ በሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎች በመለማመድ ላይ መሆናቸውን አመልክተዋል::



እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ በአውራ ወረዳ የአውራ ወንዝን በመጥለፍ ከ5 ኪሎ ሜትር በላይ ቦይ በመሥራት 2 መቶ ሄክታር መ ት ላይ 2 መቶ አባወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የእርሻ ልማት በማካሄድ ላይ ነው::

ወ/ት ኤልሳቤጥ ሚልተን የድርጅቱ የአካባቢ ልማት ባለሙያና አስተባባሪ እንደገለጹት ከእርሻ ጎን ለጎን የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ዝርያዎች የማልማትና የአፈርና የውሃ ዕቀባ

በክልሉ ኋላቀር የሥራ ባህል ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ለሥራ የሚሰለፉትም ሆነ ሥራውን የሚሠሩት ሴቶች በመሆናቸው ተጨማሪ የሥራ ጫና በሴቶች ላይ እንደሚፈጠ ር ግንዛቤ በማስጨበጥ ወንዶችም ሥራውን እንዲሰሩ ከተደረገ የአውራ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በአካባቢው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ተስፋ ሰጭ ነው ብለዋል::

## ድርጅቶቹ ከ172 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ካፒታል ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው

በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ቁጥራቸው 28 የሚሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እ.ኤ.አ ከ 2003 እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የሚቆዩ ከ 921 ሺህ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ከብር 172 ሚሊዮን በላይ ግምት ያላቸውን ፕሮጀክቶች ቀርፀው ልዩ ልዩ የግብርና እና የገጠር ልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኙ በዞኑ የገጠርና ግብርና መምሪያ የምግብ ዋስትናና የአደጋ መከላከል ባለሙያ አመለከቱ::

ባለሙያዋ ወ/ሮ የዛብነሽ ዓለሙ ሰሞኑን በሥፍራው ለተገኘው የፌዴራል አደጋ

መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ቡድን እንደገለጹት ድርጅቶቹ ከሚንቀሳቀሱባቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ በኤች አይቪ ኤድስ መከላከልና ምክር አገልግሎት በ5 ሚሊዮን 714 ሺ 622 ፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን በመንከባከብ በ22 ሚሊዮን 682 ሺህ 910 ፣ በተቀናጀ የገጠር ልማት በ5 ሚሊዮን 551 ሺህ 963፣ የአካል ጉዳተኞችን እና የከተማ ድሀ ሴቶችን መልሶ በማቋቋም በ23 ሚሊዮን 610 ሺህ 84 ፣ በንፅህ መጠ ጥ ውሃ አቅርቦትና በአካባቢ ንፅህና 12 ሚሊዮን 517 ሺህ 870 ፣ በገንዘብ ለምግብ 14 ሚሊዮን 177 ሺህ 550 ፣ በመለስተኛ የመስኖ ልማት 6 ሚሊዮን 447 ሺህ 311 ፣ በጤና እና በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች 11 ሚሊዮን 805 ሺህ 671 ፣ በትምህርትና የአቅም ግንባታ 37 ሚሊዮን 191 ሽህ 865 በመሠረተ ልማት ግንባታና በልማት ዕርዳታ 12 ሚሊዮን 380 ሺህ 583 ፣ የጦርነትና የድርቅ ተጎጂዎችን መልሶ በማቋቋም 25 ሚሊዮን 647 ሺህ 822 ብር ካፒታል ባላቸው የፕሮጀክቶች የሥራ ዘርፎች ተሰማርተዋል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመንግሥት ሊደረስባቸው በማይችሉ ቦታዎችን ሸፍነው የሚሰሩና ያላቸውም ሪሶርስ ቀላል ባለመሆኑ የኦዲትና የቁጥጥር ሥራን በማጠናከር ሥራቸውን መከታተል እንደሚገባ የገለጹት ወ/ሮ የዛብነሽ መያዶችን በልማት አጋርነት በማየት ከመንግሥት የሚፈለገው ድጋፍ ከተደረገላቸው የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በኩል የማይናቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ብለዋል።

## ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶች የአጠናን ስልት ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሄደ

ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶችን በመለየት ፣ በመተንተንና ምላሹን በማጠናከር ረገድ የሚታዩ ችግሮችንና የአጠናን ስልቶችን ለመዘርጋት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ያተኮረ ስብሰባ ነሐሴ 17 ቀን 1997ዓ.ም በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሄደ።

በዚሁ የምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶች ጥናት ስልት ለመንደፍ በአማካሪነት ከተመደቡት ከሚስ ሱለውቲዝ ጋር ባካሄዱት ስብሰባ ላይ የሥነ ምግብና ጤና ፣ የግብርና፣ የውሃና የአካባቢ ንፅህና ንዑሳን ግብረኃይሎች በየበኩላቸው በእስካሁኑ ባደረጉት እንቅስቃሴ ምግብ ነክ ያልሆኑ ፍላጎቶች ከእያንዳንዱ ግብረ ኃይል አኳያ ብያኔያቸው ምን እንደሆነ፣ በድንገተኛ ጊዜ የዕርዳታ ምላሽ ለመስጠት የመለያ መስፈርቶች መኖር አለመኖራቸው ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ፍላጎቶች ጥናት ሲካሄድ እነማንን እንደሚያካትቱና ምንጩ ከየት እንደሆነ የሀሳብ ልውውጥ ተካሂዷል።በዚሁ ላይ በመመስረትም ከአማካሪ ቡድኑ ስለሚጠበቀው የጥናት ውጤትም እያንዳንዱ ንዑስ ግብረኃይል ከየሥራ ባህርዩ አንፃር ሰፊ ሀሳብ አቅርቧል።

የግብርና ግብረኃይል ምግብ ነክ ያልሆኑ ፍላጎቶችን የሚገልፀው ፣ የሚተነትነውና የሚወስነው ችግሩ በተከሰተ ጊዜ ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የደረሰውን ጉዳትና የሚያስፈልገውን ዕርዳታ በማጥናት መሆኑን ገልጾ ፣ ፍላጎቱን ለመወሰን የሚያስችል ግልፅ የሆነ መመዘኛም ሆነ የአጠናን ዘዴ (**Methodology**) እስካሁን ድረስ እንደሌለ አብራርቷል። በአጠቃላይ በግብረ ኃይል አባላቱ ከአማካሪ ቡድኑ የሚጠብቁት በምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ፍላጎት የአጠናን ስልትና የአተገባበር ሥርዓቶች መቅረፅ ፣ የዕርዳታ ምንጮችን በመለየት የተጠናከረ የክትትል ሥርዓት የሚዘረጋበትን አሠራር ፣ የአገር ውስጥ አቅም የሚያጎለብትበትንና

አደጋው ከመከሰቱ በፊት ፍላጎቶችን የመለያ ሥልት /ዘዴ/ አጥንቶ እንዲያቀርብ መሆኑን አብራርተዋል።

የጤናና ሥነ ምግብን በተመለከተም ንዑስ ግብረኃሉ በየአሥራ አምስት ቀን በሚያደርጋቸው መመደበኛ ስብሰባዎች በእስካሁኑ በእጅ የሚገኙ ሰነዶችን በማቀናጀት፣ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በመገምገም በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ የሚከሰቱ የጤናና የሥነ ምግብ ችግሮችን በመለየት፣ በመተንተንና ለመነሻ የሚሆን መጠባበቂያ እቅድ **/Contingency plan/** ሰነድ ቢያዘጋጅም ለወደፊቱ ውጤታማ ሥራ ለማከናወን አማካሪዋ ሰነዱን በመመልከት በይበልጥ የሚጎለብትበትን ዘዴ እንዲያጠኑ ሃሳብ ቀርቧል።

አማካሪዋ ምግብ ነክ ያልሆነ ፍላጎት በአስቸኳይ ጊዜ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ እንዳለውና አሁን በኢትዮጵያ ባለው የአደጋ ፅንሰ ሀሳብ መሠረት አንዳንዶቹ ችግሮች በልማት ተቋማት፣ አንዳንዶቹ የአስቸኳይ ጊዜ ሥራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በመንግሥት እየተሰሩ መሆናቸውን መረጃዎች እንደሚያመለክቱ አብራርተዋል። በግብረ ኃይሉ የተነሱትን ሁሉንም ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባትና በተሰጠው ዝርዝር የሥራ መረሀግብር **/Term of reference/** መሠረት በተቀናጀ መልኩ ችግሩን ለማጥናት የሚያስችል ወጥ የሆነ ጥናት ለማቅረብ የተቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።